# የኢዴፓ የመቐለ ጉዞ

በመርስኤ ኪዳን

ሰኔ 19፣ 2001 ዓ.ም.

የጥላቻ ፖለቲካ የሚያበቃበትን ቀን ስንጠብቅ የነበርን ኢትዮጵያውያን ኢዴፓ ከአዲስ አበባ ውጪ በተለያዩ ከተሞች ህዝባዊ ስብሰባዎች ለማካሄድ መወሰኑ አስደስቶን ሳናበቃ በአዋሳ የተካሄደው ስብሰባ ስኬታማ መሆኑ ደግሞ የተስፋ ብርሃን ፈንጣቂ ዜና ሆኖልናል። የአማራጭ ፓርቲ ያለህ ስንል የነበርን ሰዎች የቀጣዮቹን ስብሰባዎች ውጤት በጉጉት በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን። ይህ የኢዴፓ እንቅስቃሴ የአብዛኞቻችንን ቀልብ የሳበ ሆኖ ሳለ የዛሬውን ፅሁፍ ለማቅረብ ያነሳሳኝ ደግሞ ይህ ተራማጅ ፓርቲ የገዢው ፓርቲ ደጀንና የመጨረሻ ምሽግ በሆነችው በመቐለ ከተማ ሊያደርግ ያቀደውን ህዝባዊ ስብሰባ በተመለከተ ይሆናል።

የኢዴፓ ድረ ገፅ ውስጥ ገብቼ ፓርቲው የያዛቸውን የህዝባዊ ስብሰባ እቅዶች የተመለከትኩ ሰሞን አንድ ፊልም ተመልክቼ ነበር። ፊልሙ በ1978 ዓ.ም በተወዳጁና በጀግናው የሕወሓት የጦር መሪ በሀየሎም አርአያ የተመራው በመቐለ ከተማ ከርቸሌ በእስር ይማቅቁ የነበሩ እስረኞችን የማስፈታት ታሪክ ላይ ያጠነጠነ ነበር።

በፊልሙ ላይ ሀየሎም የዚህን ዘመቻ አስፈላጊነት ሲያስረዳ ደርግን ከመሀል ደጀን ምሽጉ መምታት ከፍተኛ ታሪካዊና ስነልቦናዊ አስተዋፅዖ እንዳለው ይናገራል። እውነትም ይህ ጀግና ሰው ትክክል ነበር። ዘመቻው ከተካሄደ በሁዋላ ሕወሓት በኢትዮጵያ የትጥቅ ትግል ህዋ ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ መሆኑን ከማረጋገጡም ባሻገር ለሚታገልለት ህዝብ አለሁለህ ባይነቱን በከረቸሌ ሲንሳቀሉ የነበሩ እስረኞችን በማስፈታት አስመስክሯል።

ታዲያ ይህ ፊልም ከኢዴፓ ጋር ምን አገናኘው ትሉ ይሆናል። በእርግጥ ይህ ታሪክ በቀጥታ ከኢዴፓ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። ሆኖም በኦፕሬሽኑ ክስተትና ኢዴፓ በመቐለ ከተማ ሊያደርግ ባቀደው ስብሰባ መካከል ቁልፍ የሆኑ መመሳሰሎች አሉ። አንደኛ በጊዜው መቐለ ከተማ  እንዳየሱስ ተራራ ላይ የሚገኘው  የጦር ካምፕ የደርግ ጦር ዋነኛ የጦር እዝ እንዲሁም የመጨረሻ ምሽግ ነበር። አሁን የአሁኑ መንግስት ገዢ ፓርቲ የሆነው የሕወሓት የመጨረሻው የፖለቲካ ምሽግ ትግራይ ክልል ብሎም መቐለ ከተማ ነው። ሁለተኛ ባለራእዩ የሕወሓት የጦር መሪ ሀየሎም አርአያ በደርግ መሀል ምሽግ በመቐለ ከተማ ግፍ እየደረሰባቸው የሚገኙ ወገኖቻችንን ለማዳን እዚያው ምሽጉ ድረስ በመሄድ ጀብደኛ ሊያሰኝ የሚችል ግን ተግባራዊ የሆነ እቅድ አወጣ። አሁንም ደግሞ ባለራእዮቹ የኢዴፓ መሪዎች በትግራይ የሚገኙ ወገኖቻቸውን ድጋፍ ለማግኘት የሕወሓት መሀል ምሽግ መቐለ ከተማ ላይ ለመዝመት ጀብደኛ የሚመስል ግን ተገቢ የሆነ እቅድ ይዘዋል።

በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲህ እንዲያ እያልኩ ያምሰለሰልኩትን ሃሳብ በሁለት ጥያቄዎች ሸክፌ ወረቀት ላይ አሰፈርኩና እነሆ እያልኳችሁ ነው። የመጀመሪያው የትግራይ ህዝብና ኢዴፓ የጋራ አጀንዳ አላቸውን? ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ኢዴፓ ከትግራይ ህዝብ ጋር ያለውን ትስስር ለማጠናከር ምን ማድረግ ይጠበቅበታል? የሚሉ ናቸው።

የኢዴፓ እና የትግራይ ህዝብ የጋራ አጀንዳዎች ይሆናሉ ብዬ ያሰብኳቸው

የኢትዮጵያ አንድነት፣

የኢትዮጵያ ሉኣላዊነት እና

የትግራይ ተወላጆች ከትግራይ ውጪ ያላቸው የኑሮ ሁኔታ ናቸው።

የትግራይ ህዝብ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት የሚቆረቆር እና ይህን ሉአላዊነት ለማስከበር ከማንም በላይ መስዋዕትነትን የከፈለ ህዝብ ነው። ሲጀምርም ይህች ኢትዮጵያ እያልን የምንጠራት አገር ፍሬ ዘር የተፈጠረውም በዚሁ በትግራይ ነው። የትግራይ ህዝብ ነፃነቱና ብሔራዊ ጥቅሙ እንዲከበርለት የሚፈልገውን ያክል የአገሩ ሉኣላዊነትና አንድነት እንዲጠበቅ ይፈልጋል። ታዲያ የትግራይ ህዝብ በመሪ ድርጅቱ በሕወሓት መሪነት ባደረገው ተጋድሎ ብሄራዊ መብቱን ቢያስከብርም፣ የበለጠ ክብር የሚሰጠው ኢትዮጵያዊነቱና ኢትዮጵያዊ አንድነቱ በሚፈልገው መልኩ በሕወሓት ተከብሯል ወይም ተጠብቋል ለማለት አይቻልም። ኢዴፓ ይህን የትግራይ ህዝብ በሕወሓት ላይ ያለበትን ቅሬታ እንደ ዕድል (opportunity) መጠቀም ይኖርበታል። የትግራይ ህዝብ በ1998 ዓ.ም በተደረገው የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በብዙ ኢትዮጵያውያን መስዋእትነት የተገኘው ድል እንደ ቀልድ በአልጀርስ ስምምነት መቀልበሱ እያንገበገበው ይገኛል። ኢዴፓ በጊዜው ይህን የሕወሓት ስህተት በተመለከተ ዳር ቆሞ አስተያየት ከመስጠት ይልቅ ጉዳዩን ጉዳዬ ብሎ እንቅስቃሴ በማድረግ በሺዎች የሚቆጠሩ ደጋፊዎቹን በማሳተፍ ተቃውሞውን ማሰማቱ የሚታወስ ነው። የኢትዮጵያ ሉአላዊነት እና አንድነት የትግራይ ህዝብና የኢዴፓ የጋራ አጀንዳ መሆኑን ሌሎች ብዙ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ሂደቶችን እያጣቀሱ ማሳየት ይቻላል።

ሌላው ጉዳይ የሕወሓት በቋንቋ (ብሄር) ላይ ብቻ የተመረኮዘ ፌደራል ስርአት በዜጎች ላይ እያደረሰ ያለው ተፅእኖ ነው። በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች በነፃነት የመስራት መብታቸው ተገድቦ፣ በማያውቁት ቋንቋ እየተፈረደባቸው፣ ወገኖቻቸው የታገሉለት መብታቸው ሁሉ ተገፎ በመኖር ላይ ይገኛሉ። ይህ እውነታ በትግራይ ተወላጆች ላይ ብቻ ሳይሆን በማንኛው ከተወለደበት ክልል ውጪ በሚኖር ኢትዮጵያዊ ላይ ያለ ተፅእኖ ነው። ለምሳሌ በናዝሬት ወይም አዳማ የሚኖሩ ኦሮሞ ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን ማናቸውንም ከመንግስት ጋር የሚደረግ የስራ ግንኙነት ላይ የሚጠቀሟቸውን ዶክመንቶች በማያውቁት ቋንቋ (በኦሮምኛ) እንዲያስተረጉሙ ይገደዳሉ፣ በማያውቁት ቋንቋ ይፈረድባቸዋል፣ በብሄራዊ ማንነታቸው ይብጠለጠላሉ ወዘተ..። ትግራዮች የታገሉት አማርኛ የማይናገር ትግሬ በትግሪኛ እንዲዳኝ፣ አማርኛ የማይናገር

ኦሮሞ በኦሮሚኛ እንዲዳኝ እንጂ ነገሩ ተገልብጦ አማርኛ ተናጋሪው ተገዶ ትግሪኛ ወይም ኦሮሚኛ እንዲናገር አልነበረም። የኢ.ዴ.ፓ ፕሮግራም ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል በሚገባው ቋንቋ ካልሆነም በአንድ የጋራ ቋንቋ የመጠቀም መብቱን የሚያስከብር ነው። ኢ.ዴ.ፓ በፕሮግራሙ እንዳሰፈረው ይህን የተዛባ ፌደራላዊ ስርአት በህጋዊ መንገድ መቀየር አጀንዳው ነው።

ኢ.ዴ.ፓ ከትግራይ ህዝብ ጋር የሚጋራቸው ከዚህም በላይ ብዙ አጀንዳዎች እንዳሉ ጥርጣሬ የለውም። ታዲያ በነዚህ የጋራ አጀንዳዎች ይህን ህዝብ ለማሰለፍ ኢ.ዴ.ፓ ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?

ኢ.ዴ.ፓ በፓርቲው ዙሪያ ያሉ ብዥታዎችን ማጥራት፣ የብሄር ብሄረሰቦችን ስጋት መጋራትና መቅረፍ እና የድርጅቱን አባላት ብሄራዊ ስብጥር ማብዛት ከቻለ ከኢ.ህአዴግ ውጪ ብቸኛው አገርን መምራት የሚችል አማራጭ ፓርቲ ሆኖ መውጣት ይችላል ብዬ አምናለሁ።

ኢ.ዴ.ፓን በተመለከተ በህዝቡ ዘንድ ብዙ ብዥታዎች አሉ። ትግራይ ውስጥ በኢ.ህአዴግ ደጋፊዎች ዘንድ ኢ.ዴ.ፓን እንደ የድሮ ስርአቶች (በዋነኝነት የኢ.ሰ.ፓ) ቅሪት አድርጎ የማየት አዝማሚያ አለ። ይህ ሊፈጠር የቻለው በእርግጥም በኢ.ዴ.ፓ ውስጥ ብዙ የቀድሞ የኢ.ሰ.ፓ አባላት ከመኖራቸው በመነጨ እናም ኢ.ህአዴግ ይህን ቁንፅላዊ ሀቅ አጋኖ በመደስኩሩ የመጣ ነው። ሌላው አመለካከት ኢ.ዴ.ፓን የአማራ ጥቅም አራማጅ ፓርቲ አድርጎ የመመልከት ነው። ይህም ከኢ.ዴ.ፓ መሰረታዊ አመጣጥ የሚመነጭ ነው። ኢ.ዴ.ፓ የመአህድ ወጣት ክንፍ በነበሩ ወጣቶች የተመሰረተ ፓርቲ እንደሆነ ማንም የሚያውቀው ሀቅ ነው። ሆኖም ፓርቲው ከጊዜ ወደ ጊዜ ህብረብሄራዊነቱን ለማጠናከር ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህ ህብረብሄራዊነት በኢ.ዴ.ፓ ውስጥ በበቂ ሁኔታ አለ ለማለት ግን ያስቸግራል።

ኢ.ዴ.ፓ የተለያዩ ብሄሮች አባላትን ለማሳተፍ በመጀመሪያ ደረጃ የነኚህን ብሄሮች ልብትርታ ማዳመጥና ደስታቸውንም ሆነ ችግሮቻቸውን መጋራት ይገባዋል። ለምሳሌ በችግር ጊዜ መድረስ ሲባል በድርቅ ጊዜ እህል ወይም ገንዘብ ማዋጣት፣ በቦታው ተገኝቶ ለመርዳት መሞከር፣ ችግሩን ለፖለቲካ ጥቅም ከማዋል ይልቅ ችግሩ እንዲቀረፍ እርዳታ ማፈላለግ ሊሆን ይችላል። ደስታ መካፈል ሲባል በበአላት መሳተፍ (ለምሳሌ በኢሬቻ በአል በመሳተፍ ለኦሮሞ ባህል ያለውን አክብሮት መግለፅ) ሊሆን ይችላል። የልማት ማህበሮችን መደገፍ፣ የተፈጥሮ እንክብካቤ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ (ዛፍ ተከላ)፣ ባህላዊ እሴቶችን ማክበር እና የመሳሰሉት ተግባራትን ማከናወን የህዝቦች የአለኝታነትን ያሳያል። በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች እነኚህን የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች ማድረግ ከተቻለ ብዙ ብሄሮችን ማሰለፍ ይቻላል።

ኢ.ዴ.ፓ ወደ መቐለ ሲያቀና ለነኚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ አዘጋጅቶ ሊሆን ይገባዋል። በፓርቲው ዙሪያ ያሉ ብዥታዎችን ከማጥራት እና አላማውን ከማብራራት ባሻገር ወያነ በመባል ለሚታወቀው የትግራይ ህዝብ ትግል ተገቢውን ክብር

መስጠት፣ በዚህ ትግል ለተሰዉ ሰማእታት ተገቢውን ክብር መስጠት፣ የትግራይ ወጣቶች በፓርቲው የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ መጋበዝ ሊደረጉ የሚገባቸው ተግባሮች ናቸው ብዬ አምናለሁ።

በዚህ አጋጣሚ በመቐለ በሚካሄደው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ የሚገኙ ሁሉም የኢዴፓ አመራር አባላት አንድ አንድ ዛፍ በመትከል ወገንተኝነታቸውን እንዲያሳዩ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ኢዴፓ ስብሰባ በሚያካሂድባት በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ከተማ እያንዳንዱ አባል አንድ አንድ ዛፍ እንዲተክል ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ሰላም!

አስተያየትዎን በemail ይለግሱኝ mersea.kidan@gmail.com

በመርስኤ ኪዳን

ሰኔ 19፣ 2001 ዓ.ም

ሚኒያፖሊስ፣ ሚኔሶታ

ሀገረ አሜሪካ